# ትምህርት 40

1. ሳዖል በእግዚአብሔር ላይ ባመፀ ጊዜ ቀጣዩ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን እግዚአብሔር የመረጠው ማንን ነበር?

ሀ- ዳዊትን።

2. ሳዖልና ዳዊት የሚለያዩት እንዴት ነበር?

ሀ- ሳዖል ከእግዚአብሔር ተለይቶ በኃጢአት እንደ ተወለደ አላመነም ነበር ዳዊት ግን አመነ።

ለ- ሳዖል እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ አላመነም ነበር ዳዊት ግን አመነ።

ሐ- ሳዖል እግዚአብሔር ብቻ ሊያድነው እንደሚችል አላመነም ነበር ዳዊት ግን አመነ።

መ- ሳዖል እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ የገባውን የተስፋ ቃል አላመነም ነበር ዳዊት ግን አመነ።

3. ዳዊት የራሱን ቤት ሠርቶ ካጠናቀቀ በኋላ ምን ለመሥራት ፈለገ?

ሀ- ዳዊት ለእግዚአብሔር ቤት ለመሥራት ፈለገ።

4. ለእግዚአብሔር ቤት የሚሠራው ማን ነበር?

ሀ- የዳዊት ልጅ ሰሎሞን።

5. እግዚአብሔር ለዳዊት የገባው ታላቅ የተስፋ ቃል ምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር አዳኙን ከዳዊት ዘር እንደሚልክ ቃል ገባ።

6. ሰሎሞን ለእግዚአብሔር የሠራው ቤተ መቅደስ እስራኤላውያን በበረሃ ለእግዚአብሔር ከሠሩት የማደሪያ ድንኳን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነበር?

ሀ- የማደሪያው ድንኳንም ሆነ የቤተ መቅደሱ የመጀመሪያ ክፍል ቅድስት ይባል ነበር።

ለ- የማደሪያው ድንኳንም ሆነ የቤተመቅደሱ ሁለተኛ ክፍል ቅድስተ ቅዱሳን ይባል ነበር።

ሐ- የማደሪያው ድንኳንም ሆነ ቤተ መቅደሱ ሁለቱንም ክፍሎቻቸውን የሚለይ መጋረጃ ነበራቸው።

7. እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነና ኃጢአትን ሁሉ ስለሚጠላ ሊቀ ካሕኑ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ምን ያደርግ ነበር?

ሀ- የእንስሳትን ደም በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ ይረጭ ነበር።

8. እግዚአብሔር ሊቀ ካሕኑ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ የረጨውን ደም ሲመለከት ምን ያደርግ ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ለቀጣዩ ተጨማሪ ዓመት የተሻለ መሥዋዕት እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ሕዝቡን በኃጢአቱ ከመቅጣት ይቆጠብ ነበር።

9. የእንስሳት ደም የሰዎችን ኃጢአት ሊያስወግድ የማይችለው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም የኃጢአት ዋጋ የሚከፈለው በኃጢአተኛው ሞት ስለሆነ ነው።

10. ንጉስ ሰለሞን ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን ምን ደረሰባቸው?

ሀ- እስራኤላውያን ቀጣዩ ንጉሥ ማን መሆን እንዳለበት አልተስማሙም ነበር ስለዚህ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ተከፋፍለው ሁለት ሕዝቦች ሆኑ።

11. በሰሜን የሚገኙት ዐሥር ነገዶች ምን ተብለው ተጠሩ?

ሀ- እስራኤል።

12. በደቡብ የሚገኙት ሁለት ነገዶች ምን ተብለው ተጠሩ?

ሀ- ይሁዳ።

- እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለሰዎች የሚናገረው ለምንድን ነው?

- ሰዎች እንዲድኑ።

- እግዚአብሔር ሰዎች ይድኑ ዘንድ እንዲነግሯቸው ለሰዎች መልእክቱን ይሰጣል።

- እግዚአብሔር መልእክቱን ለኖኅ ሰጠው ኖኅም ይድኑ ዘንድ ለሕዝቡ መልእክቱን ነገራቸው።

- እግዚአብሔር መልእክቱን ለሙሴ ሰጠው ሙሴም ይድኑ ዘንድ ለፈርዖንና ለግብፃውያን መልእክቱን ነገራቸው።

- እግዚአብሔር መልእክቱን ለኢያሱ ሰጠው ኢያሱም ይድኑ ዘንድ ለእስራኤላውያን መልእክቱን ነገራቸው።

- አንድ ቀን እግዚአብሔር ዮናስ የሚባል እስራኤላዊ ጠራ።

- እግዚአብሔር መልእክቱን ለዮናስ ሰጠው ዮናስንም ነነዌ በሚባል ከተማ ወደሚኖሩ እጅግ ክፉ ወደ ሆኑት ሰዎች መልእክቱን እንዲያደርስለት አዘዘው።

- ነነዌ ከተማ የሚኖሩት ሰዎች አሦራውያን ይባሉ ነበር።

ዮናስ 1፡1-3ሀ

1- የእግዚአብሔር ቃል ወደ አማቴ ልጅ ወደ ዮናስ እንዲህ ሲል መጣ፤

2- ክፋቷ በእኔ ፊት ወጥቶአልና ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሄደህ፣ በእርሷ ላይ ስበክ።

3- ዮናስ ግን ከእግዚአብሔር ፊት ኰበለለ፤ ወደ ተርሴስም ለመሄድ ተነሣ።

- እግዚአብሔር ዮናስ ወደ ነነዌ ከተማ እንዲሄድ የፈለገው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የነነዌን ሕዝብ ስለ ወደደ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር የነነዌን ሕዝብ ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ሊያድናቸው ስለፈለገ ነው።

- ዮናስ የኮበለለው ለምን ነበር?
- ዮናስ የኰበለለው ወደ ነነዌ ከተማ መሄድ ስላልፈለገ ነው።

- ዮናስ ወደ ነነዌ መሄድ ያልፈለገው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም የነነዌ ሰዎች በጣም ክፉዎች ስለነበሩ ነው።

- ምክንያቱም የነነዌ ሰዎች የእስራኤላውያን ጠላቶች ስለነበሩ ነው።

- ምክንቱም ዮናስ እግዚአብሔር የነነዌን ሕዝብ እንዲያድን ስላልፈልገ ነው።

- ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት መኰብለል ችሎ ነበር?

ዮናስ 1፡3-10

3- ዮናስ ወደ ኢዮጴ ወረደ፣ ወደዚያው ወደ ተርሴስ የምትሄድ መርከብም አገኘ። የጉዞውንም ዋጋ ከከፈለ በኋላ፣ ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተርሴስ ለመኮብለል ተሳፈረ።

4- እግዚአብሔርም በባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስን ላከ፤ ከባድ ማዕበልም ተነሥቶ መርከቢቱን አንገላታት፤ ልትሰበርም ተቃረበች።

5- መርከበኞቹ ሁሉ ፈሩ፤ እያንዳንዱም ሰው ወደ አምላኩ ጮኸ፤ የመርከቢቱም ክብደት እንዲቀል፣ በውስጧ የነበረውን ዕቃ ወደ ባሕሩ ጣሉት። ዮናስ ግን ወደ መርከቢቱ ታችኛ ክፍል ወርዶ ተኛ፤ በከባድም እንቅልፍ ላይ ነበር።

6- የመርከቢቱም አዛዥ ወደ እርሱ ሄዶ፣ «እንዴት ትተኛለህ? ተነሥና አምላክህን ጥራ እንጂ፣ ምናልባትም ያስበንና ከጥፋት ያድነን ይሆናል» አለው።

7- ከዚያም መርከበኞቹ እርስ በርሳቸው፣ «ይህ ክፉ ነገር በማን ምክንያት እንደ መጣብን ለማወቅ፣ ኑ፣ ዕጣ እንጣጣል» ተባባሉ። ዕጣም ተጣጣሉ፤ ዕጣውም በዮናስ ላይ ወደቀ።

8- ከዚያም፣ «ይህ ሁሉ አስጨናቂ ነገር በማን ምክንያት እንደ መጣብን ንገረን፤ ሥራህ ምንድን ነው? ከወዴትስ መጣህ? አገርህስ የት ነው? ከየትኛውስ ሕዝብ ነህ?» አሉት።

9- እርሱም፣ «እኔ ዕብራዊ ነኝ፤ የብስንና ባሕርን የፈጠረውን፣ የሰማይን አምላክ እግዚአብሔርን አመልካለሁ» አለ።

10- ዮናስ እርሱ አስቀድሞ ነግሮአቸው ስለ ነበር፣ ከእግዚአብሔር እንደ ኰበለለ ዐወቁ፣ ስለዚህም በሁኔታው በመደንገጥ፣ «ይህ ያደረግኸው ምንድን ነው?» አሉት።

- ዮናስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መኰብለል ችሎ ነበር?
- አልቻለም።

- ዮናስ ከእግዚአብሔር መደበቅ ችሎ ነበር?
- አልቻለም።

- ዮናስ ከእግዚአብሔር ማምለጥ ችሎ ነበር?

- አልቻለም።

- ማንም ከእግዚአብሔር ማምለጥ አይችልም።

- ሰይጣንና አጋንንቱም እንኳ ከእግዚአብሔር ማምለጥ አይችሉም።

ዮናስ 1፡11-17

11- የባሕሩም ማዕበል እጅግ እየበረታ ስለ ሄደ፣ «ባሕሩ ጸጥ እንዲልልን በአንተ ላይ ምን ብናደርግ ይሻላል?» አሉት።

12- እርሱም፣ «ይህ ታላቅ ማዕበል በእኔ ምክንያት እንደ መጣባችሁ አውቃለሁ፤ አንሥታችሁ ወደ ባሕሩ ጣሉኝ። ባሕሩም ጸጥ ይላል» አላቸው።

13- ሰዎቹ ግን ባላቸው ኀይል እየቀዘፉ ወደ የብስ ለመጠጋት ሞከሩ፤ ይሁን እንጂ አልቻሉም፤ ባሕሩ የባሰ ይናወጥ ነበርና።

14- «እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ በዚህ ሰው ነፍስ ምክንያት አታጥፋን፤ የዚህ ንጹሕ ሰው ደምም በእኛ ላይ አይሁን፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ የወደድኸውን አድርገሃልና» ብለው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ።

15- ከዚያም ዮናስን ይዘው ወደ ባሕሩ ጣሉት፤ ባሕሩም ከመናወጥ ጸጥ አለ።

16- ሰዎቹም እግዚአብሔርን እጅግ ፈሩ፤ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትም አቀረቡ፤ ለእርሱም ስእለትን ተሳሉ።

17- እግዚአብሔር ግን ዮናስን የሚውጥ ትልቅ ዓሣ አዘጋጀ፤ ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት አደረ።

- ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ በማመጽ ወደ ነነዌ ስላልሄደ፣ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

- እግዚአብሔር ዮናስን እንዲውጥ ትልቅ ዓሣ ላከ።

- ዮናስ በትልቁ ዓሣ ሆድ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ቆየ?
- ለሦስት ቀንና ለሦስት ሌሊት።

- ዮናስ በትልቁ ዓሣ ሆድ ውስጥ ሆኖ ራሱን ማዳን ችሎ ነበር?
- አልቻለም።

- ዮናስን ማዳን የቻለው ብቸኛው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር።

- ሰዎች ከዮናስ ጋር የሚመሳሰሉት በምንድን ነው?

- ዮናስ በትልቁ ዓሣ ሆድ ውስጥ ሆኖ ራሱን ማዳን እንዳልቻለ ሁሉ፣

- ሁሉም ሰዎች ራሳቸውን ከኃጢአት ከሞትና ከሰይጣን ኃይል ማዳን አይችሉም።

- እግዚአብሔር ብቻ ዮናስን ማዳን እንደ ቻለ ሁሉ ሰዎችን ሁሉ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- በትልቁ ዓሣ ሆድ ውስጥ ዮናስ ምን አደረገ?

ዮናስ 2፥1

1- ዮናስ በዓሣው ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

- ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ ማመጹን ለእግዚአብሔር ገለጸ።

- ዮናስ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት መሥራቱን ለእግዚአብሔር ገለጸ።

- ዮናስ እንዲያድነው ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።

- እግዚአብሔር ዮናስን አዳነው?

ዮናስ 2፥10

10 - እግዚአብሔር ዓሣውን አዘዘው፤ ዮናስንም በደረቅ ምድር ላይ ተፋው።

- ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ ማመፁንና ኃጢአት መሥራቱን በተረዳ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

- እግዚአብሔር ትልቁ ዓሣ ዮናስን በደረቅ መሬት ላይ እንዲተፋው አደረገ።

- እግዚአብሔር ዮናስን ለምን አዳነው?

- ምክንያቱም ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ ማመፁን ስላመነ።
- ምክንያቱም ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱን ስላመነ።

- እግዚአብሔር ዮናስን ካዳነው በኋላ «ወደ ነነዌ መሄድ የለብህም» አለው?

- አላለውም።

ዮናስ 3፥1-2

1- የእግዚአብሔርም ቃል ለሁለተኛ ጊዜ እንዲህ ሲል ወደ ዮናስ መጣ፤

2- «ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ ሄደህ የምነግርህን መልእክት ስበክላት። »

- እግዚአብሔር አይለወጥም።
- እግዚአብሔር በፍጹም አይለውጥም።

- እግዚአብሔር አሁንም ዮናስ መልእክቱን ይዞ ወደ ነነዌ ሰዎች እንዲሄድ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር አሁንም የነነዌን ሰዎች ማዳን ይፈልጋል።

- በዚህስ ጊዜ ዮናስ እግዚአብሔርን ታዝዞ ወደ ነነዌ ሄዷል?

ዮናስ 3፡3-5 & 10

3- ዮናስም የእግዚአብሔርን ቃል ታዘዘ፤ ወደ ነነዌም ሄደ። በዚህ ጊዜ ነነዌ ታላቅ ከተማ ነበረች፤ እርሷንም ከዳር እስከ ዳር ለመጐብኘት ሦስት ቀን ያስፈልግ ነበር።

4- ዮናስም ወደ ከተማዪቱ ገብቶ የመጀመሪያውን ቀን ከተጓዘ በኋላ «ነነዌ በአርባ ቀን ውስጥ ትገለበጣለች» ብሎ ዐወጀ።

5- የነነዌም ሰዎች እግዚአብሔርን አመኑ፤ ጾምንም ዐወጁ፤ ሰዎቹም ሁሉ ከትልቁ እስከ ትንሹ ማቅ ለበሱ።

10- እግዚአብሔርም ምን እንዳደረጉና ከክፉ መንገዳቸው እንዴት እንደ ተመለሱ ባየ ጊዜ ራራላቸው፤ በእነርሱም ላይ ሊያመጣ ያሰበውን ጥፋት አላደረገም።

- በዚህ ጊዜ ዮናስ እግዚአብሔርን ታዝዞ ወደ ነነዌ ሄደ።

- በዚህ ጊዜ ዮናስ የእግዚአብሔርን መልእክት ለነነዌ ሕዝብ አደረሰ።

- ዮናስ የነነዌ ሕዝብ የኃጢአትን መንገድ ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ ተናገረ።

- የነነዌ ሕዝብ ዮናስ የነገራቸውን የእግዚአብሔር ቃል ሰሙ?
- አዎን።

- እግዚአብሔር እናንተም እንደ ነነዌ ሰዎች እንድትሆኑ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር እናንተም እንደ ነነዌ ሰዎች መልእክቱን እንድታደምጡ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር እናንተም እንደ ነነዌ ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል እንድታምኑ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር የኃጢአት መንገድ ትታችሁ የእግዚአብሔርን መንገድ እንድትከተሉ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር ሌሎች ብዙ ሰዎች የእርሱ መልእክተኞች እንዲ ሆኑና ቃሉን ለሰዎች እንዲነግሩ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር የእርሱ መልእክተኞች እንዲሆኑና መልእክቱን ለሰዎች እንዲነግሩ የመረጣቸው ሰዎች ምን ይባሉ ነበር?

- ነቢያት።

- እግዚአብሔር አንዳንዶቹን ነቢያት ወደ ዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች ላካቸው።

- እግዚአብሔር አንዳንዶቹን ነቢያት ደግሞ ወደ ሁለቱ የይሁዳ ነገዶች ላካቸው።

- ነቢያት ለሕዝቡ ምን ተናገሩ?

- የኃጢአትን መንገድ እንዲተዉና የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተሉ።

- እንዲሁም ነቢያቱ እግዚአብሔር ሕዝቡ ጣዖቶቻቸውን እንዲያስወግዱ እንደሚፈልግ ተናገሩ።

- ከእግዚአብሔር ነቢያት አንዱ ኢሳይያስ ይባል ነበር።

- ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች ሄደ።

- እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አማካይነት ለዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች የተናገረው ይህን ነው፥

ኢሳይያስ 10፥6

6- እግዚአብሔር እንዲህ አለ «ሀብታቸውን እንዲዘርፍ፣ ምርኮን እንዲያግበሰብስ፣ እንደ መንገድ ላይ ጭቃም እንዲረግጣቸው፣ አምላክ በሌለው ሕዝብ ላይ እልከዋለሁ፣ በሚያስቈጣኝም ሕዝብ ላይ እሰደዋለሁ፤»

- ዐሥሩ የእስራኤል ነገዶች የኃጢአት መንገዳቸውን ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ ካልተከተሉ ምን ይደርስባቸዋል?

- እግዚአብሔር ዐሥሩን የእስራኤል ነገዶች እንዲያሸንፉና ባሪያዎች እንዲያደርጓቸው አሦራውያንን ይልክባቸዋል።

- ሌላው ከእግዚአብሔር ነቢያት አንዱ ኤርምያስ የሚባል ነበር።

- ነቢዩ ኤርምያስ ወደ ሁለቱ የይሁዳ ነገድ ሕዝቦች ሄደ፡

- እግዚአብሔር በነቢዩ በኤርምያስ አማካይነት ለሁለቱ የይሁዳ ነገዶች የተናገረው ቃል ይህ ነው፡-

ኤርምያስ 20፡5

5- እግዚአብሔር እንዲህ አለ «የዚህችን ከተማ ሀብት ሁሉ፣ ጥሪቷን፣ የይሁዳን ነገሥታት ውድ ዕቃና ንብረት ሁሉ ለጠላቶቻቸው አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እነርሱም ዘርፈው ወደ ባቢሎን ይዘውት ይሄዳሉ።»

- ሁለቱ የይሁዳ ነገዶች የኃጢአት መንገዳቸውን ትተው የእግዚአብሔርን መንገድ ካልተከተሉ ምን ይደርስባቸዋል?

- እግዚአብሔር ሁለቱን የይሁዳ ነገዶች እንዲያሸንፏቸውና ባሪያዎቻቸው እንዲያደርጓቸው ባቢሎናውያንን ይልክባቸዋል።

- እግዚአብሔር አልተለወጠም።

- እግዚአብሔር አሁንም ሁሉም ሰው የኃጢአትን መንገድ ትቶ የእግዚአብሔርን መንገድ እንዲከተል ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር የኃጢአትን መንገድ ትተው የእርሱን መንገድ ያልተከተሉትን ሁሉ በዘለዓለም ሞት ይቀጣቸዋል።